# *አቤቱታ ለአንድነት ሃይል የተቃዋሚ የራዲዮ ጣቢያዎች*

*ከአገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን*

*ከካርቱም ሱዳን*

የኢትዮጵያ ህዝብ ለወያኔ አልገዛም ብሎ በመሰለውና አቅሙ በፈቀደው መጠን ሁሉ ወያኔን እየተፋለመ ነው፡፡ በኛ እምነት ይህ ህዝባዊ አመፅ ቀጥሎ ወያኔን ማንበርከከ መቻል አለበት፡፡ እስካሁን የኢትዮጵያ ህዝብ አያሌ የትግል ምራፎችን ቢጀምርም በተደጋጋሚ በአምባገነኖች ተኮላሽቷል፡፡ ይህ በየጊዜው መኮላሸት ደግሞ ለአምባገነኖች የልብ ልብ ስጥቶ ዛሬ በወያኔ እንደምናየው አልጋ ላይ የዋሉ በሽተኞች፤ እመጫቶችን ፤ ጨቅላ ህፃናትና አረጋውያን እናት አባቶችን ሳይቀር በጅምላ ሲጨፈጨፉ የምናይበት ዘመን ላይ ደርሰናል፡፡ ወያኔ ህዝባችንን በተለይም ወጣቱን በቀሳፊው ኤድስ ለመጨረስም በአንድ ምላጭ ከሃያ በላይ ሰዎችን የሚላጭና ጉልበታቸው የተላላጠና የደማ ወጣቶችን በደሙ ላይ በእምብርክክ እያስከደ የኤድስ ቫይረስ የሚተላለፍበትን ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ተወዳዳሪ የሌለው ወንጀል እንዲፈፅም አስችሎታል፡፡ የእስካሁኑን የህዝባችን ትግል ከሚኮላሸባቸው ምክንያቶች የታጋዩ ወገን ከጠላት አንፃር ሲታይ የዝግጅትና የአመራር ክፍተት በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው ፡፡ ዛሬ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጦርነት ላይ ነው ፡፡ ህዝቡ ይህን ጦርነት ባሸናፊነት ሊወጣ ይጠበቃል ፡፡ በዚህ በያዝነው ሰላማዊ ህዝባዊ አመፅም ሁለት ክፍተቶች/ ጉድለቶች ይፋ ሁነው ተስተውለዋል፡፡ እነሱም አንደኛ የወጥ የሆነ የዜና የኢንፎርሜሽ እጥረት ሁለተኛ የተነሳውን የህዝብ ማእበል አቅጣጫ የማስያዝና አመራር የመስጠት ናቸው ፡፡ ውዥንብር አለ፡፡ ሆን ተብሎ ህዝብን ለመከፋፍል የሚነዛውን ከትክክለኛው መለየት የሚያስቸግርበት ሁኔታም አለ ፡፡ ህዝብ ለትግል መነሳሳቱን ምክንያት አድርጎ የህዝብ ጆሮ ለመሳብ የሌለ ቀቢፀ ተስፋ እየነዙ የልመና ኮረጆን ለመሙላት የሚደረግ ሩጫ አለ፡፡ የአንድነት ሃይል ድርጅቶችን ለመከፋፈል የሚነዛ መርዝ አለ፡፡ በወያኔ ሰራሽ ቅንጅት ሊያደናግሩ የሚሞክሩ በአካባቢያችን ሳይቀር ብቅ ብለዋል ፡፡ ወያኔን በመታገል ስም የሻቢያን ሌላ ዙር ወጥመድ ቅዱስ አድርጎ የማቅርብ ብዥታም አለ፡፡ እነዚህን ለአብነት የጠቀስናቸውንና መስል ችግሮችን ማስወገድ የሚቻለው ህዝቡ በወቅቱ ውጥ ዜናና ኢንፎርሜሽን እንዲሁም ከተገቢው ህጋዊ አካል አመራር ማግኘት ሲቻል ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ያሉንን የመገናኛ ብዙሃን በአግባቡና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ልንጠቀምባቸው ስንችል ነው፡፡ ብክነት አለ፡፡

የዚህ አቤቱታችንም ዋና አላማ እነዚህ ክፍተቶች ትኩረት አግኝተው የሚመለከታቸው እንዲያስቡበትና ትኩረት እንዲሰጡት ለማሳሰብ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ህዝብ ዋና ዋና የዜናና ኢንፎርሜሽን ምንጮች

1) የራዲዮ ጣቢያዎች 2) የነፃው ፕሬስ ውጤቶች 3) የዘመኑ ተክኖሎጂ ውጤት የሆኑት የኤሌክትሮኒክስ / ኢንተርኔት ሜዲያ ናቸው፡፡ የኛ ትኩረት ግን በራዲዮ ጣቢያዎች ላይ ነው ፡፡ ለራዲዮ ትኩረት መስጠታችንም የነፃው ፕሬስም ሆነ የኤሊክትሮኒክ የመገናኛ ብዙሃን የየራሳቸው ጠቀሜታ ቢኖራቸውም ከራዲዮ ጋር በፍፁም ሊነፃፀር አለመቻል ነው ፡፡ ሌላውን ትተን በከተማ በገጠሩ የተማረው ሆነ ያልተማረው በቀላሉ ሊከታተለው የሚችለው ራዲዮ በመሆኑ ነው ፡፡ የተቃዋሚ የራዲዮ ጣቢያዎች( ባለቤትነታቸው የፖለቲካ ድርጅቶች ሆኑ ግለሰቦች ) ላይ ማተኮራችንም የአሜሪካም ሆነ የጀርመን ድምፅ ራዲዮ ጣቢያዎች የመንግስቶቻቸውን አቋም ተከትለው ሊለወጡ ስለሚችሉ ነው፡፡ ( በነገራችን ላይ የጀርመን ድምፅ አሁን አዲስ አባባ ላይ ዘጋቢ አለው ማለት አይቻልም፡፡ የአሜሪካ ድምፅም ከአዲስ አበባ ውጭ ያለውን የአገሪቱ ክፍል መድረስ እንዳልቻሉ ይታያል፡፡ ) ብዙው የወያኔ ወንጀል ገና አልተጋለጠም፡፡ ወያኔ በገጠሩ ህዝብና በገበሬው ላይ የሚፈፅመው ሰቆቃ አልተዘገበም፡፡ የመገናኛ ብዙሃን ድመክታቸውን ካላስተካከሉ ይኸው ይቀጥላል፡፡ የከተሚው ብሶትና ችግር ይሰማል፡፡ የገጠሩ ተቀብሮ ይቀራል፡፡

ሁሉንም ህዝብ መድረስ የሚችል የራዲዮ ስርጭ ምን ያህል ጠቀሜታ እንዳለው በአሁኑ ህዝባዊ መነሳሳት የራዲዮ ጣቢያዎች የተጫወቱት ሚና ምስክር ነው። የአሜሪካ ድምፅ ፣ የትንሣኤ ራዲዮ፣ ፍኖተ ዴሞክራሲ፣ የጀርመን ድምፅና ሌሎችም የተጫዎቱት ሚና በአርአያነታቸው የሚጠቀሱ ናቸው ። ሁላችንም እንደምናውቀው በዛ ያሉ በተቃዋሚ ድርጅቶችና አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን የሚንቀሳቀሱ የራዲዮ ጣቢያዎች አሉ። እነዚህ የራዲዮ ጣቢያዎች ጥረታቸውን ቢያስተባብሩ የበለጠ መስራት ይችላሉ ትግሉንም አንድ እርከን ከፍ ያደርጋሉ ብለን እናምናለን። ከዚህ በፊት እንደገለፅነው የተቃዋሚ የመገናኛ ብዙሃን የጋራ መርሃ ግብር ሊነድፉ ይገባል እንላለን። ህዝቡ በየወቅቱ ትኩስ ዜናዎችን ሊያገኝ የሚልችልበትን መንገድ በጋራ ቢቀይሱ ይበልጥ ትግሉን ያግዛሉ። የተቃዋሚ የራዲዮ ጣቢያዎች ከዜና ኢንፎርሜሽን በተጨማሪ ያላቸውን የአየር ሰአት የትግሉን አቅጣጫ ጠቋሚና ፈር ቀዳጅ የትንተና ፅሁፎችና ዝግጅቶች ሊያቀርቡ ይጠበቃል። የያዝነውን የትግል መሳሪያ በአግባቡ እንጠቀም ስንል አንዱ ይህን ማለታችን ነው። ለዚህ ደግሞ የሚመለከታቸው ተቀራርበው መነጋገር መወያነየታቸው የመጀመሪያው ርምጃ ነው ።

በሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚደመጡ ራዲዮ ጣቢያዎች ለትግሉ አቅጣጫና አመራር ለመስጠት ይችላሉ። በአሁኑ ወቅት የአመራር ክፍተት ይታያል። ለዚህ በምክንያትነት ከሚጠቀሱት አንደኛ አብዛኛዎቹ የቅንጅት አመራሮች በመታሰራቸው ፣ ሁለተኛ የህበረቱ ሊቃነመናብርት የነበሩት የዲሞክራሲያዊ ስርአት መሰረት የሆነውን የብዙሃን ድምፅን ረግጠው ትርጉመ ቢሱ ፓርላማ በመግባታቸው ሶስተኛ በቅርበት አመራር ሊሡጡ የሚችሉ ሌሎች የህብረቱ መሪዎች ህገወጥ ተብለው በመፈረጃቸው አራተኛ ከእስር የተረፈው የቅንጅት አመራር ከህብረቱ ጋር በጋራ ትግሉን ማቀናጀት አለመቻል ከሚታዩት ጥቂቶቹ ናቸው። የራዲዮ ጣቢያዎች ከላይ የተጠቀሱትን እና ሌሎች የአመራር ክፍተቶችን የመሙላት ሚና ሊጫዎቱ ይገባቸዋል። እነዚህ የራዲዮ ጣቢያዎች ህዝቡ ከምሁራን ፣ ከተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች፣ ከፖለቲካ ተንታኞና ከሃያሲያን አቅጣጫ ጠቋሚና ፈርቀዳጅ ሃሳቦችን ሲቻል በቃለ መጠይቅ መልክ ያለበለዚያም በፅሁፍ ሊያቀርቡ የሚችሉበትን መንገድ ሊፈጠሩ ይገባል እንላለን ። የአሁኑ ህዝባዊ አመፅና ትግሉ በየተራ ሆኖ ለወያኔ ዱላ ያመቸበት አንዱ ምክንያት የአመራር ክፍተት ነው። የአዲስ አበባ ህዝብ ሶስት ቀን ሙሉ በውያኔ ሲጨፈጨፍ በተቀረው የኢትዮጵያ ክፍል ይህ ነው የተባለ መነሳሳት አልነበረም ። ምክንያቱ በቅርብ ሆኖ ትግሉን ማስተባበር አልመቻል ነው። አመፁ ወደተቀረው የአገሪቱ ክፍል የተስፋፋው የአዲስ አበባ ህዝብ ተጨፍጭፎ እንዴት እኛ ዝም እንላለን በሚል በራሱ አነሳሽነት ለወያኔ በሚያመች ሁኔታ ተራ በተራ ተነሳ እንጂ በተቃዋሚ ድርጅቶች አለመመራቱ በገሃድ የታየ ነው። የራዲዮ ጣቢያዎች የጋራ አጀንዳ እና መርህ ኖሯቸው የዜናና ኢንፎርሜሽን ልውውጥ ቢኖራቸው ህዝቡ ሁሉንም የራዲዮ ጣቢያዎች የሚደመጡበት ሁኔታ ይፈጠራል። የራዲዮ ጣቢያዎች የሚፎካከሩበት ሳይሆን ተደጋግፈው የህዝቡን የላንፎርሜሽን እጥረት መቅረፍ ይጠበቅባቸዋል። ይህ በበኩሉ የራዲዮ ጣቢያዎችም ከድርጅት/ቡድን አጥር ወጥተው የሚታዩበት የበለጠ አድማጭና ተሳትፎ የሚያገኙበት ሁኔታ ይፈጥራል። ለትግሉ እንደ አንድ የአመራርና አቅጣጫ መሰጫ መሳሪያዎች የሚታዩበትን እድል ያሰፋዋል ብለን እናስባለን። በመሆኑም የኢትዮጵያን አንድነት የሚደግፉ የተቃዋሚ የራዲዮ ጣቢያዎች በሙሉ በተለይም የአጭር ሞገድ የራዲዮ ስርጭት ላላችው ድርጅቶችንና/ስብሰቦች/ግለሰቦች አቤቱታችንን እናቀርባለን።

ሃሳባችንን የሚጋሩ አገር ወዳድ ወገኖች ለሚመለከታቸው ምክርና ሃሳብ እንዲሰጡ እናሳሰባለን።

አንድነታችን ይጠንክር !

ትግሉ ይፋፋም!

አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን

ከካርቱም